# የምግብ አቅርቦትና ስርጭት ወቅታዊ ሪፖርት

ታህሳስ 23 ቀን 2002 ዓ.ም

## 1. የምግብ አቅርቦት

### 1.1. ለአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ምግብ ዕርዳታ ተጠቃሚዎች

1.1.1. *መንግሥትና አጋሮቹ በጋራ እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 2009 ይፋ ባደረጉት የዕርዳታ ፍላጐት ሰነድ መሠረት እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር እስከ ዲሰምበር 2009 በአለው ጊዜ የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ምግብ ዕርዳታ አቅርቦት ድጋፍ የሚሻ ሕዝብ ቁጥር 6.2 ሚሊዮን ያህል ነበር፡፡*

1.1.2. በ6ኛው ዙር ማለትም(በጥቅምት/ህዳር 2002 ዓ.ም.) ለተደረገ የስርጭት እንቅስቃሴ እስከ ታህሣሥ 07 ቀን 2002 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በመንግሥት፣ በመያዶችና በዓለም ምግብ ኘሮግራም ለ5.7 ሚሊዮን ተረጂዎች 99,515 ሜ/ቶን ምግብ ተመድቦ እስከአሁን 92,249.70 ሜ.ቶን ተጓጉዟል፡፡ *(በየክልሉ የተጓጓዘ የምግብ መጠን በሰንጠረዥ 1 ተመልክቷል)፡፡*

1.1.3. የ7ኛው ዙር ማለትም፣ የታህሣሥ ወር 2002 የዕርዳታ ድልድል የተካሄደው በኦሮሚያ ፣ በሶማሌ ፣ በአማራ ፣ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፣ በጋምቤላ ፣ በትግራይ ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ፣ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትና በድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር ውስጥ ለሚገኙ 5.5 ሚሊዮን ያህል ሰዎች ነው፡፡ የተመደበው የዕርዳታ መጠንም 95,712 ሜ/ቶን ሲሆን ከዚህ ውስጥ 38,614 ሜ/ቶን በመንግሥት፣ 22,191 ሜ/ቶን በዓለም ምግብ ኘሮግራም እና ቀሪው 34,907 ሜ/ቶን ደግሞመንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በኩል የሚሠራጭ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት እስካሁን ለትግራይ 11,106 ሜ/ቶን፣ ለአማራ 13,889.9 ሜ/ቶን ፣ ለኦሮሚያ 10,627 ሜ/ቶን ፣ ለሶማሌ 13,305 ሜ/ቶን ፣ ለደቡብ 5,324 ሜ/ቶን ፣ ለቤንሻንጉል 250 ሜ/ቶን ፣ ለጋምቤላ 498 ሜ/ቶን ለድሬዳዋ 142 ሜ/ቶን በጠቅላላው 55,142.9 ሜ/ቶን ተጓጉዟል፡፡ ቀሪውንም 40,570 ሜ/ቶን በተያዘው የስርጭት ኘሮግራም መሠረት አጓጉዞ ለማጠናቀቅ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ነው፡፡

## 2. በ2010 የሚኖር የምግብ ክምችት

- አሁን በመጋዘን ውስጥ ያለውን የምግብ ክምችትና ከውጭ ሀገር በመግባት ላይ የሚገኘውንና በቀጣይም እንደሚገባ የሚጠበቀውን የዕርዳታ ምግብ ከግምት ውስጥ በማስገባት በ7ኛው ዙር መሰራጨት የሚገባውን ምግብ በማሰራጨት በያዝነው እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 2010

ጀምሮ ላለው ጊዜ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል 272 ሺህ በላይ ሜ/ቶን ምግብ እንደሚኖር ተገምቷል፡፡

- እህል ከወደብ ተጓጉዞ ወደ አገር ውስጥ እስኪገባ ድረስ የእርዳታ አቅርቦት እንቅስቃሴው እንዳይስተጓጎል በብድር መልክ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል 155,499.48 ቶን የምግብ ክምችት በመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር ይገኛል፡፡
- በመስከረም/ጥቅምት 2002 ዓ.ም. በመንግሥትና በአጋር ድርጅቶች በጋራ በተደረገው ቅድመ መኸር (mid meher) ግምገማ መሠረት በቀጣዩ ዓመት ማለትም እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ እስከ ጁን 2010 የሚኖረው የተረጂ ቁጥር 4.76 ሚሊዮን እንደሚሆን ተገምቷል፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ እንዲቻል በህዳር/ታህሳስ የመስክ ጥናት እንዲካሄድ የተደረገ በመሆኑ በዚሁ ጥናት የተረጋገጠው የአስቸኳይ ጊዜ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ ድጋፍ የሚያስፈልገው የተረጂ ቁጥር በቅርቡ (በጥር ወር 2002 ዓ.ም.) ይፋ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ እስከዚያው ድረስ ግን የዕርዳታ ድጋፍ ለማቅረብ ይኸው ከላይ የተጠቀሰው 4.76 ሚሊዮን የተረጂ ቁጥር ጥቅም ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

## 3. ወደአገር ውስጥ ይገባል ተብሎ የሚጠበቅ የዕርዳታ እህል መጠን

- በጅቡቲ ወደብ በኩል የገባና የሚገባ የዕርዳታ ምግብን በሚመለከት፡-
  - ⇒ በጅቡቲ ወደብ በኩል አንድ መርከብ 24,000 ሜ/ቶን ስንዴና ማሽላ ይዛ በመግባት በማራገፍ ላይ ትገኛለች፡፡ ይሄው ዕርዳታ ወደ አገር ውስጥ ተጓጉዞ በካቶሊክ ዕርዳታ ድርጅት (CRS) መጋዘን የሚገባ ይሆናል፡፡ እንዲሁም 51,400 ሜ.ቶን ስንዴ የጫነች መርከብ የማራገፍ ሥራ ጀምራለች፡፡ ዕርዳታው በዓለም ምግብ ኘሮግራም እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስር ወደሚገኙ መጋዘኖች በቅርቡ እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡
- በሌሎች ወደቦች በኩል የሚገባውን ዕርዳታ በተመለከተ
  - ⇒ በበርበራ ወደብ በኩል 23,486 ሜ/ቶን ያህል ስንዴ የያዘች መርከብ ማራገፍ የጀመረች ሲሆን እህሉም ወደ አገር ውስጥ እየገባ ይገኛል፡፡
  - ⇒ በፖርት ሱዳን በኩል የሚገባውን እህል በተመለከተ ደግሞ ቀደም ሲል 16,256 ሜ/ቶን እህል ይዛ የገባችው መርከብ የማራገፍ ሥራዋን አከናውና እህሉን ወደ አገር ውስጥ የማጓጓዙ ሥራም ተጠናቋል፡፡

## በልዩ ሁኔታ ስለቀረበ የአስቸኳይ ጊዜ የዕለት ዕርዳታ ምግብ

### 3.1. በተለያዩ ምክንያቶች ከሕዝብ መፈናቀል ጋር በተያያዘ፣

- በኦሮሚያ ክልል በባሌ ዞን በጉራዳሞሌ ወረዳ በሰው ሰራሽ ችግር ምክንያት ለተፈናቀሉ 8,581 ወገኖች የሚሠራጭ 1,287 ኩንታል እህልና 39 ኩንታል የምግብ ዘይት ተጠይቆ በመ/ቤቱ

አምስት ተሽከርካሪዎች 690 ኩንታል እህልና 39 ኩንታል የምግብ ዘይት እንዲደርሳቸው ተደርጓል፡፡ ቀሪውም ምግብ በመጓጓዝ ላይ ይገኛል፡፡

## 4. መንግስት ከአጋሮቹ ጋር በጋራ ኦክቶበር 22 ቀን 2009 ይፋ በአደረገው የዕርዳታ ጥሪ መሠረት የተሰጠ ምላሽ

1. **የካናዳ መንግሥት፣** ግምቱ የአሜሪካን ዶላር 9.2 ሚሊዮን የሆነና ለ7ኛ ዙር የሚውል ከ15 ሺህ ቶን በላይ ምግብ፤
2. **የአውሮፓ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፣** ግምቱ የአሜሪካን ዶላር 18 ሚሊዮን ያህል የሆነ ከ 31 ሺህ ቶን በላይ ምግብ (ከዚህ ውስጥ 16 ሺህ ቶን ያህል ለመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ብድር ለመክፈል ተመላሽ ነው)፤
3. **የእንግሊዝ መንግሥት፣** ግምቱ 4 ሚሊዮን ዶላር የሚሆንና እ.ኤ.አ ለ2010 የሚውል 6 ሺህ ቶን አልሚ ምግብ፤
4. **የአውስትራሊያ መንግሥት፣** ግምቱ የአሜሪካን ዶላር 1.96 ሚሊዮን የሆነና ለ7ኛ ዙር የሚውል ከ 2.9 ሺህ ቶን በላይ ምግብ፤
5. **እ.ኤ.አ ለ2010 የአሜሪካን መንግሥት፣** ጠቅላላ ግምቱ 133 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ የሆነ 201, 760 ቶን (ማለትም፣157,760 ቶን በዓለም ምግብ ፕሮግራም በኩል፣ 44 ሺህ ቶን ደግሞ በመያድ በኩል) ለመለገስ ቃል የገባ ሲሆን ዕርዳታውም እ.ኤ.አ.ከፌብሩዋሪ እስከ ኤፕሪል 2010 በአለው ጊዜ ወደ ሀገር ውስጥ እንደሚገባ ይጠበቃል፡፡

**ዕዝል**

## ለአስቸኳይ የዕለት ዕርዳታ ተጠቃሚዎች የተጓጓዘ ምግብ (በሜትሪክ ቶን)

### ሀ) በ6ኛ ዙር (ጥቅምት/ህዳር 2002 ዓ.ም)

| ክልል | የተመደበ እህል | | | ጠቅላላ የተመደበ | እስካሁን የተጓጓዘ | አፈጻጸም በመቶኛ | የተጠቃሚ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በመንግስት | በአለም ምግብ ፕሮግራም (Habs and Spokes System) | በመያዶች | | | | |
| ትግራይ | 12,045.1 | | | 12,045.1 | 12,045.1 | 100 | 747,466 |
| አፋር | 1,210.3 | | | 1,210.3 | 1,210.3 | 100 | 74,412 |
| አማራ | 15,817.1 | | | 15,817.1 | 15,817.1 | 100 | 985,669 |
| ኦሮሚያ | 16,460.9 | | 4,998.5 | 21,459.4 | 21,456.7 | 99.99 | 1,286,876 |
| ሶማሌ | 6,491.1 | 24,412.90 | | 30,904.0 | 24,206.4 | 78.33 | 1,520,129 |
| ደቡብ ብ/ብ/ሕ | 10,084 | | 6,031.5 | 16,115.5 | 16,115.5 | 100 | 1,061,179 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 565.5 | | | 565.49 | 565.49 | 100 | 35,232 |
| ጋምቤላ | 1,275.9 | | | 1,275.9 | 1,275.9 | 100 | 79,503 |
| ድሬዳዋ | | | 122.7 | 122.7 | 122.7 | 100.0 | 7,944 |
| **ድምር** | **63,949.90** | **24,412.90** | **11,152.7** | **99,515.50** | **92,249.70** | **93** | **5,798,410** |

### ለ) በ7ኛ ዙር (ታህሳስ/2002 ዓ.ም)

| ክልል | የተመደበ እህል | | | ጠቅላላ የተመደበ | እስካሁን የተጓጓዘ | አፈጻጸም በመቶኛ | የተጠቃሚ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በመንግስት | በአለም ምግብ ፕሮግራም (Habs and Spokes System) | በመያዶች | | | | |
| ትግራይ | 2,322 | | 11,106 | 13,428 | 11,106 | 83 | 684,304 |
| አፋር | 1,164 | | | 1,164 | | 0 | 75,412 |
| አማራ | 6,591 | | 8,553 | 15,144 | 13,889.9 | 92 | 1,013,827 |
| ኦሮሚያ | 15,105 | | 8,528 | 23,633 | 10,627 | 45 | 1,360,551 |
| ሶማሌ | 3,952 | 22,191 | 756 | 26,899 | 13,305 | 49 | 1,412,369 |
| ደቡብ ብ/ብ/ሕ | 8,133 | | 5,324 | 13,457 | 5,324 | 40 | 801,324 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 529 | | 0 | 529 | 250 | 47 | 35,232 |
| ጋምቤላ | 818 | | 498 | 1,316 | 498 | 38 | 79,503 |
| ድሬዳዋ | -- | | 142 | 142 | 142 | 100 | 7,644 |
| **ድምር** | **38,614** | **22,191** | **34,907** | **95,712** | **55,142** | **58** | **5,470,166** |


ስልክ ቁ. 0115509666 ፋክስ. 0115525111 ኢሜል. info.officer@dppc.gov.et ዌብሳይት. www.dppc.gov.et ፖ.ሳ.ቁ 5686 አዲስ አበባ